

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከኦክቶበር 11-20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከኦክቶበር 21-31 እና ከኖቬምበር 1-10/2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉ ከመምጣታቸዉ ጋር ተያይዞ፤ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የሀገሪቱ አከባቢዎች በመጨረሻዎቹ ስድስት ቀናቶች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡ ፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ሶማሌ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ጠንከር ያለ የደመና ክምችት ተስተውሎባቸዋል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎችም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባ ምንጭ 23.3፣ 41.7፣ ጎሬ 55.6፣ 32.4፣ ነገሌ 34.5፣ ነቀምት 26.2፣ አቦምሳ 25፣ አልጌ 40፣ አማን 24.3፣ አንገር ጉትን 20.6፣ አርጆ 20.2፣ 41.4፣ አየሁ 31.8፣ 21፣ አይከል 28.2፣ ቦሬ 46.2፣ 22.7፣ 22.3፣ ቡለን 38.2. 38.2፣ ቡሬ 41፣ ቻግኒ 24.6፣ ጨዋቃ 25፣ 24.4፣ ጭራ 23.4፣ 21፣ ዲላ 35፣ ዶሎመና 30.3፣ ፉኙዶ 25፣ 20.6፣ 22.8፣ ጋምቤላ 51.8፣ ጋቲራ 20.8፣ ጊምቢ 23.1፣ 27.7፣ ቡሌ ሆራ 40፣ ጂራ 25.6፣ ጂንካ 24.2፣ ካቺሴ 35.5፣ ቀብሪ ዳሀር 24.4፣ ላይብር 26፣ 27.7፣ ሊሙ ገነት 42.7፣ 39.4፣ ማጂ 24፣ 31፣ 25፣ ማሻ 90.2፣ 20.5፣ ምዕራብ አባያ 37፣ ነጆ 24.2፣ ፓዌ 38.5፣ ሳዉላ 28.7፣ ተርጫ 22.9፣ 28.8፣ 42፣ ወራቤ 21.8፣ ያቤሎ 34.6፣ 43.2፣ ኢጋሮ 33፣ አሺ 25.5፣ አሸሪ 23.4፣ አታንጎ 21.5፣ 46.5፣ ቢላም ቢሎ 22.2፣ 44.6፣ ቡልቂ 22.4፣ ዳራማሎ 20.1፣ ጉበቲ 33.6፣ 21፣ ሀመሮ 20.7፣ ሀንቲ 31.4፣ ቅዳሜ ገበያ 48.6፣ 56.7፣ 46.3፣ 59.8፣ 26.6፣ 37.8፣ 28.9፣ ኩሚ 22.5፣ መርጦ ለማሪያም 23.3፣ ሙጊ 26.9፣ ኦንጋ 29.6፣ ሸንዲ 22.5፣ ትንሹ ሜጢ 36.8፣ 28.6፣ መንደር አስራ አንድ 96፣ ያንፋ 28.3፣ 38.4፣ 48.2፣ 22.3፣ 30.3፣ 43.5 እንዲሁም ይርጋጨፌ 20.4፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በሰላሳ ሶስት (33) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታች በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ

አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.0 - 96 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ45 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል መንደር አስራ አንድ፣ ማሻ፣ ያቤሎ፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ጎሬ፣ ጋምቤላ፣ ያንፋ፣ አታንጎ፣ ቦሬ፣ ቢላም ቢሎ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጥን ያለዉ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 )፡፡





ምስል፡1 ከኦክቶበር 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር ዞኖች ላይ ከ31-250 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ምዕራብ ጎጃም፣የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ31-342 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

በሌላ በኩል የሰሜን፣ መከከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፋንቲ፣ ሃሪና ጋቢ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ስልጤ፣ ከንባታ፣ የሃላባ፣ የም፣ ቀቤና ዞኖች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከ6-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ከሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ላሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንዲሁም ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ለሆኑት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ ያለው እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚያከናውኑ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ነበረ። እንዲሁም በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ቆላማው አካባቢ ለሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በቂ የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኦክቶበር ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ መካከለኛው እና በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በታችኛው አባይ እና ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሀ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አባይ እንዲሁም በላይኛው ገናሌ ዳዋ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደ ሲሆን በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት እንደ ዋቢ ሸበሌ እና ግልገል ጊቤ 3 ግድቦች የሚገባውን ውሃ መጠን ከመጨመር አኳያ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ የተቀሩት የአፋር ደናክል፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ተከዜ እና አባይ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ሰር ነበሩ፡፡ (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፤ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በኦክቶበር እና በመጀመሪያዎቹ በኖቬምበር አስር ቀናት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ነው። በመደበኛ ሁኔታ በሀገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ የበጋ ወቅት ዝናብ ከኦክቶበር መጀመሪያዎቹ ቀናቶች ጀምሮ መዝነብ ይጀምራል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በይበልጥ በምዕራብና በደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡ ፡ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን በተለይም በደጋማ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ እየጨመረ ይሄዳሉ፡፡


### 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና የምስራቅ ቦረና፣ የምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት ደቡብ ምዕራብ እና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ

የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31, 2025 የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ነጎብ፣ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

| የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| | ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | ምዕራብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣የሰሜን እና ምዕራብ ጎጃም የአዊ፣ እና | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
| አማራ | በጥቂት የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | በጥቂት የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት የጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የዝናቡ መጠንና ስርጭት ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

በመጪዎቹ የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋንና ክምችት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅትን ዝናብ እያገኙ በነበሩት  በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና የሰሜን የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ ፡፡

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### 2.3  እ.ኢ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው ቀጣይነት ያለዉ እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ዞኖች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት በወቅቱ ለሚጀምረው የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግ አሉታዊ ሁኔታን ለመቀነስና መልካም አጋጣሚዎችን በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

ሠንጠረ ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ ፣ የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞን፣ የሰሜንና ምዕራብ ጎጃም፣ ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች<br>• ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>• ውሃ አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት | • የደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ሊደረስ ይችላል<br>• እንደ ዋግና የመሳሰሉ የሰብል በሽታዎች መከሰት | • የሚኖረውን ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ እና ስንዴ የመሳሰሉ ሰብሎችን መሰብሰብ<br>• የሰብል ማሳዎችን በቅርበት መከታተል ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር ተግባራዊ ማድረግ |
| **የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ ፣ ምስራቅ ባሌ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች ፣ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ፣ ሰብሎች የዉሀ ፍላጎት መሟላት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት<br>• ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት | • በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል<br>• እንደ ዋግ የመሳሰሉ የሰብለ በሽታ መከሰት | • የሚኖረውን ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም የደረሱ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ እና ስንዴ የመሳሰሉ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ<br>• የሰብል ማሳዎችን በቅርበት በመከታተል ፀረ-ተባይና ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር ተግባራዊ ማድረግ |
| ጉራጌ፣፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ የድህረሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን | | • የደረሱ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ |
| **በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች እና ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ነጎብ፣ ዞኖች ፣ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ ፣ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማከማቸት<br>• ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል | • ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ<br>• የደረሱ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በኦክቶበር ሶስተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው የበጋ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሰሆን የተቀሩት ተፋሰሶች ዝቅተኛ እርጥበት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግ አሉታዊ ሁኔታን ለመቀነስና መልካም አጋጣሚዎችን በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውሀ ተፋሰሶች | የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ መካከለኛውና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ላይኛው እና መካከለኛ ገናሌ ዳዋ፣ ላይኛውና መካከለኛ ዋቢ ሸበሌ፣ ታችኛ ኦጋዴን፣ መካከለኛው እና ታችኛው አባይ እና በታችኛ ተከዜ | መካከለኛ የእርጥበት መጠን | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ ግድቦች የውሀ አቅርቦት መሻሻል<br>• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መጨመር<br>• የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን መጨመር | | • የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br>• የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችን ና ምክረ ሀሳቦችን በየ ጊዜው መከታተል |
| በአብዛኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ ላይኛው አባይ እና ተከዜ፣ ታችኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • በጎርፍ ሆነ በደለል ስጋት አለ መኖር<br>• በከፍተኛ ሁኔታ የሙሉ ግድቦች ላይ የነበረው ጫና መቀነስ<br>• የጎርፍ ሰጋት አለመኖር | • እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት መከላከል<br>• የተጽኖ ትንበያን መከታተል |